'ወንጀላቸውን ይፋ ከሚያደርጉ በስተቀር ሁሉም ህዝቦቼ ይማርላቸዋል።

ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: እንዲህ አለ: "የአላህ መልክተኛ
(የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፦ 'ወንጀላቸውን ይፋ ከሚያደርጉ በስተቀር ሁሉም ህዝቦቼ ይማርላቸዋል። ይፋ ከማውጣትም መካከል ሰውዬው ምሽት ላይ አንድ ወንጀልን ይሰራል ከዚያም አላህ ለርሱ (ወንጀሉን) ሸሽጎለት አንግቶ
ሳለ ‹እከሌ ሆይ! ትናንት ምሽት እንዲህ እንዲህ ሰራሁ።› ይላል። ጌታው (ወንጀሉን) ሸሽጎለት አድሮ ሳለ የአላህን ግርዶሽ ከራሱ ላይ የሚገፍ ሆኖ ያነጋል።"
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሙስሊም ወንጀለኛ ወንጀሉን በፉከራና በብልግና ይፋ የሚያወጣ ካልሆነ በቀር የአላህን ይቅርታና ምህረት የማግኘት ተስፋ እንዳለው ገለፁ። ወንጀሉን ይፋ የሚያደርግ ግን ይቅርታ አይገባውም። ምሽት ላይ ወንጀል ይሰራል ከዚያም አላህ ሸሽጎለት አንግቶ ሳለ ለሌላ ሰው ትናንት የሆነች ወንጀልን እንደሰራ ይናገራል። ጌታው ሸሽጎለት አድሮ ሳለ የአላህን ግርዶሽ የገለጠ ሆኖ ያነጋል።

https://sunnah.global/hadeeth/am/show/3756